# የአምላክ ሰው መሆን አስፈላጊነት




የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት የሰው ልጆችን ታሪክ የለወጠ፤ የሰው ልጅ ከዘለዓለም ሞት ሊያመልጥ የሚችልበትን መንገድ የከፈተ ክንውን ነው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረን እግዚአብሔር አምላክ ሰማይና ምድርን ከፈጠረበት ጥበብ አምላክ ሰው የሆነበት ጥበብ እጅግ ድንቅ እንደሆነ ነው። ለዚህም ነው የሰው ልጆች ይህንን የጌታችንን ልደት ትልቅ ቦታ ሰጥተነው ዘመናትን ስንቆጥር ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን ዓመተ ፍዳ ከልደቱ በኋላ ያለውን ዘመን ደግሞ ዓመተ ምኅረት ብለን የምንጠራው። በተጨማሪም የአምላክን ልደት ልዩ የሚያደርገው አምላክ ከመንበሩ ወርዶ የሰውን ሥጋ በመልበስ እኛን ስላከበረንና በእርሱ ሰው መሆን ድኅነትን ብሎም የመንግሥቱ ወራሽነት ስልጣን ስለተሰጠን ነው።

ቤተ ክርስቲያናችን ምስጢረ ሥጋዌ ብላ የምታስተምረን የአምላክ ባሕርይ ሰውን መዋሐዱ ነው። ይህም በአጭሩ ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ለክብሩና ለመለኮታዊ ግርማው ወሰን የሌለው አምላክ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ሰው የመሆኑ ምስጢር ነው። (ኢሳ 7፥14)። አምላክ ሰው የሆነበት ዋናው ምክንያት በኃጢአት ምክንያት ወድቆ የነበረ አዳምን ወደ ቀደመው ክብሩ ለመመለስ ነው። እግዚአብሔር አዳምን ፈጥሮ በገነት ሲያኖረው በሁሉ ላይ ስልጣንን ሰጥቶት ከአንዲት የሕይወት ዛፍ ግን እንዳይበላ አዝዞት ነበር። ከዚህች ዛፍ የበላ እንደሆነ በዚያች በበላባት ቀን ሞትን እንደሚሞት እግዚአብሔር አስቀድሞ አስታውቆት ነበር። (ዘፍ 2፥17)። ነገር ግን ተንኮለኛው ሰይጣን ከዚህች ዛፍ እንድትበላ ሔዋንን አጓጓት አታለላትም። ከተከለከለችው ዛፍ ፍሬ በላች አዳምንም አበላች። ስለሆነም አዳምና ሔዋን የአምካቸውን ትእዛዝ ተላለፉ ሕጉንም አፈረሱ። በዚህ ምክንያት የእግዚአብሔር ፍርድ ይፈጸም ዘንድ አዳምና ሔዋን መሞት ነበረባቸው። የአምላክ ትእዛዙና ፍርዱ ፍፁምና የማይታጠፍ በመሆኑ አዳምና ሔዋን ከእነሱም በኋላ ያለው የሰው ልጅ በሙሉ ከሞት ፍርድ የማያመልጥ ሆነ። መሞት ማለት ደግሞ ከእግዚአብሔር መለየት ስለሆነ በእግዚአብሔርና በፍጥረቱ በሰው ዘር መካከል የጥል ግድግዳ ኖረ።

እግዚአብሔር ግን ፍጥረቱ ጠፍቶ እንዳይቀር የሚፈልግ ድንቅ አምላክ ነውና የጠፋውን በግ አዳምን ሊታደገው ወደደ። እግዚአብሔር ምኅረቱን ሊፈጽም ሲፈቅድ ግን በአዳም ጥፋትና መተላለፍ የመጣውን ፍርድ ወይም ሞት መከፈሉ ግን ግድ ነበር።

እግዚአብሔር አዳምን ሊምረው ለምን ወደደ? የአዳም ሞት እንደተደነገገ ቢቀር ሊያስከትል የሚችላቸውን ጥያቄዎች ቀጥሎ እንመልከት።

1. <u>በእግዚአብሔር ይቅር ባይነት ላይ</u> - አዳም ኃጢአትን የሠራው በሰይጣን ተታልሎ በመሆኑ
2. <u>በእግዚአብሔር ክብር ላይ</u> - እግዚአብሔር አዳምን በራሱ አምሳል ሠራው በፍጥረታት ሁሉ ላይ እንዲገዛ ስልጣንን ሰጠው። ታዲያ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ አዳም እንዴት እንዲህ በቀላሉ ዋጋ ያጣ ሆኖ ይቀራል?
3. <u>በእግዚአብሔር ጥበብ ላይ</u> - እግዚአብሔር በረቂቅ ጥበቡ የሰውን ልጅ ሲፈጥር የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ፍቅርና በረከት ፍጹም ደስታን እያገኘ የልጅነት ስልጣኑን አክብሮ እንዲይዝ ነበር የተፈጠረው። ታዲያ እንዴት ነው ሰይጣን እነዚህን ስጦታዎች ከአዳም ሊነጥቅ የተቻለው? ቅዱስ አትናቴዎስ በዚህ ጥያቄ ላይ ሲያሰላስል «የሰው ልጅ የተፈረደበትን ታለቅ ቅጣት ከሚቀበል ይልቅ ቀድሞውኑ ባይፈጠር ይሻለው ነበር» ብሎ ነበር።
4. <u>በእግዚአብሔር ኃይል ላይ</u> - እግዚአብሔር አዳምን ሲፈጥረው ፈጥሮ ሊተወው ወይም ከሰይጣን ተንኮል ላይከላከለው ወዶ አልነበረም። ኃይል ሁሉ የእርሱ በመሆኑ በሰይጣን ላይ የበላይነት ያለው እግዚአብሔር ነውና በሰይጣን ድል ሊነሳ የማይችል አምላክ ነው። «ኃይል ክብር ምስጋና ያን ናትና» (የአባታችን ሆይ ጸሎት)።

ስለሆነም የሰው ልጅ በራሱ ባለእዕዳ ስለሆነ ራሱን ለማዳን አይችልም። ፍጥረትም ሆነ እንስሳም መላእክትም አዳኝ ሊሆኑ አይችሉም። ምክንያቱም ሰው ለበደለው በደል እራሱ ሰው መክፈል ይኖርበታልና። ነገር ግን ዕዳውን ሊከፍል የሚችል ንጹሕ ሰው ባለመገኘቱ አምላክ ሰው ሆኖ በተዋሕዶ የሰውን ሥጋ ለብሶ ሊያድነን መምጣት ነበረበት።

## ለሰው ልጅ ቤዛ (ዕዳ ከፍይ) ሆኖ አምላክ እንዲመጣ የሆነበት ምክንያት፥

1. <u>ሁሉን ቻይነቱ</u> - የእኛን የደካሞቹን የሰው ልጆች የኃጢአታችንን ሁሉ ዋጋ ለመክፈል የሚቻለው ቅድስናው የማይመረመር ፍጹም አምላክ እርሱ ብቻ በመሆኑ፤
2. <u>ሰው ሆኖ መገለጹ</u> - ፍጹም አምላክ እንደመሆኑ ሁሉ ፍጹም ሰው በመሆኑ የሰው ልጆችን ቅጣት ወስዶ ፍዳችንን ተቀብሎ በአደባባይ ለሞት ለመሰጠት የሚችል እርሱ ብቻ በመሆኑ፤ (ጢሞ 3፥16)።
3. <u>ድኅነት በምስጢረ ሥጋዌ መገኘቱ</u> - የሰው ልጅ ኃጢአትን የሠራው ፍጹም በሆነው በአምላኩ ፊት በመሆኑና ለሠራውና ለሚሠራው ኃጢአት ሊከፈል የሚገባውን የሞት ቅጣት ተቀብሎ የሰው ልጅ በራሱ ራሱን ማዳን አልተቻለውም። የሰውን ልጅ ከዘለዓለማዊ ሞት ለማዳን የሚችል ራሱን መስዋዕት አድርጎ መስዋዕትም ተቀባይ ሆኖ መቅረብ የሚችል ከእግዚአብሔር ከራሱ ሌላ ማንም ባለመኖሩ፤
4. <u>ለድኅነት የሚያስፈልገው</u> - የእግዚአብሔር ፍርድ የሰውን ልጅ ኃጢአት ለማስተሰረይ የሚችል አዳኝ ሊሆን የሚገባው ብሎ ያስቀመጠው፥
   ሀ) <u>ንጹሕ፣ ቅዱስ እና ኃጢአት የሌለበት</u> - እንደሚታወቀው የሰው ልጅ በኃጢአት ስለወደቀ እነዚህን ለማሟላት አይቻለውም። (ሮሜ 3፥12)።
   ለ) <u>ከሃሊ የሆነ</u> - የሰውን ልጅ ያሳተውን ዲያቢሎስን ለመርታት የሚችል ብርቱ፣ ሁሉ የሚቻለውና ኃያል መሆን ነበረበት። የሰይጣንን እራስ ለመቀጥቀጥ የሚቻለው ሰው ወይም ሌላ ፍጥረት ሳይሆን ከሃሊ የሆነ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ሐ) <u>የሰው ባሕርይ ያለው</u> - የእግዚአብሔር ፍርድ የተወሰነው በሰው ላይ በመሆኑ ቅጣቱን የሚቀበለው ከሰው ዘር መሆን ስላለበት፤ እንስሳትም ሆኑ መላእክት ያንን ፍርድ ለመቀበል ብቁ ባለመሆናቸው።

መ) <u>ለሰው ልጅ ለመሞት ፈቃደኛ የሆነ</u> - እግዚአብሔር የራሱ ቃልና ፍርድ ይፈጸም ዘንድ ይቅርታውን ለመፈጸም ማንንም ለማስገደድ አላስፈለገውም። እግዚአብሔር ዓለሙን እንዲሁ ወዶታልና፤ የሚከፈለውም ዋጋ በውዴታ የሆነ የእግዚአብሔርን ፍጹምና ዘለዓለማዊ ፍቅር የሚገልጽ መሆን ነበረበት። ይህንንም ማድረግ የሚቻለው ራሱ ፈጣሪ ብቻ በመሆኑ የእርሱ ሰው ሆኖ መገለጽ (ምስጢረ ሥጋዌ መከናወኑ) ግድ ነበር። የሰውን ልጅ ከዘለዓለም ሞት ለማዳን የሚቻለው ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ባለመኖሩ ኃጢአት የሌለበት አምላክ የኃጢአተኛውን የሰውን ልጅ ሥጋ ለበሰ፣ ከድንግል ማርያም ተወለደ፣ እንደ ሰው ተመላለሰ፣ የሰውን ልጅ ዕዳ ለመክፈል ወደዚህ ዓለም መጣ።

## በአምላክ ሰው መሆን ያገኘነው በረከት፥

1) ልጆቹ አደረገን .... ገላቲያ 4፣4-5
2) የክብሩ ወራሾች እንድንሆን አበቃን - ዕብ 6፥4
3) አዲስ ሰው አድርጎናል - «አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፍታችሁታልና፥ የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል» (ቆላ 3፥9-10)። የእኛን ሥጋ ለብሶ ሞትን ድል በማድረጉ እኛን አክብሮናል ለእኛም የመንፈስን ኃይል ሰጥቶናል። (የሐዋ ሥራ 1፥8)።
4) የእግዚአብሔር ቅርበት ለሰዎች - እግዚአብሔር ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ሰው ሆኖ ተመላልሶ ለሰው ልጅ ተገልጾአል። (1ኛ ዮሐ 1፥1)።
5) ሰላም በምድር ታውጇል - (ሉቃ 2፥13-14)።

ስለዚህ አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ እኛ ሰው ሆኖ ለዓለም የተገለጸበት የልደቱ ቀን የደኅንነታችን ሥራ የተጀመረበት በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ቀን እያሰበች ታላቅ በዓል አድርጋ ታከብረዋለች። ለዓለም በሙሉ ይደመጥ ዘንድ ሰው ሆኖ በቀራንዮ የተሰቀለው ለሰው ልጆች ሁሉ ቤዛ የሆነው ጌታዋ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን ታውጃለች፤ ትመሰክራለች። ዳግም እንደሚመጣ ትናገራለች። ሆኖም ግን እንደ ቀድሞው ራሱን ዝቅ አድርጎ በግርግም ሊተኛ፣ ሊፈረድበት፣ ሊተፋበት፣ ሊገደል ሳይሆን በሕያዋንና በሙታን ላይ ለመፍረድ በክብርና በጌትነት እንደሚመጣ በዚያም ቀን ጻድቃንን በቀኙ፣ ኃጥአንን በግራው እንደሚያቆም ትሰብካለች። ጌታዋና አምላኳም ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያውና ዘለዓለማዊ እንደሆነም ትመሰክራለች።

በዚህ የልደቱ መታሰቢያ በዓል ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቀደመ ክብራችን ይመልሰን ዘንድ ሥጋችንን ለብሶ ስለመጣ እያመሰገነው፤ በቸርነቱ ያሰበን ዘንድ ዳግመኛ በመጣ ጊዜ እንዳናፍር በቀኙ ለመቆም እንድንችል ያበቃን ዘንድ ተግተን እንለምነው።
ለድኅነት ምክንያት የሆነች የወላዲተ አምላክ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምልጃ እና ልመና አይለየን።

«ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ» (ሉቃ 2፥14)።

*Inspired by an article "the Need for the Incarnation" from www.suscopts.org January 2007*